የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፴፰
አዲስ አበባ–መጋቢት ፲፪ ቀን ፲፱፻፺፭

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

9th Year No. 38
ADDIS ABABA-21st March, 2003

## ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፹፭/፲፱፻፺፭ ዓ·ም የዕለት ደራሽ የእርዳታ ትራንስፖርት ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት (ማሻሻያ) ደንብ........................ ገፅ ፪ሺ፩፻፱

## CONTENTS

Council of Ministers Regulations No. 85/2003 Emergency Relief Transport Enterprise Establishment Council of Ministers (Amendment) Regulations ............................................. Page 2109

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፹፭/፲፱፻፺፭
## የዕለት ደራሽ የእርዳታ ትራንስፖርት ድርጅት ማቋቋሚያ ደንብን ለማሻሻል የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን ባወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፹፯ አንቀጽ ፭ እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯(፩)(ሀ) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የዕለት ደራሽ የእርዳታ ትራንስፖርት ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት (ማሻሻያ) ደንብ ቁጥር ፹፭/፲፱፻፺፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· ማሻሻያ

የዕለት ደራሽ የእርዳታ ትራንስፖርት ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፳፩/፲፱፻፺ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፤

አንቀጽ ፭ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፭ ተተክቷል፣

"፭· ካፒታል

ለድርጅቱ የተፈቀደው ካፒታል ብር ፶፰ሚሊዮን፫፻፲፰ሺ፯፻፶፭ ከ፹፫ ሳንቲም (ሃምሳ ስምንት ሚሊዮን ሦስት መቶ አሥራ ስምንት ሺህ ሰባት መቶ ሃምሳ አምስት ብር ከሰማንያ ሦስት ሳንቲም) ሲሆን ይኸውም በጥሬ ገንዘብና በዓይነት በሙሉ ተከፍሏል።"

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS No. 85/2003
## COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS TO AMEND THE ESTABLISHMENT OF EMERGENCY RELIEF TRANSPORT ENTERPRISE

These Regulations are Issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 4/1995 and Article 47(1) (a) of Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

1. *Short Title*

These Regulations may be cited as the "Emergency Relief Transport Enterprise Establishment Council of Ministers (Amendment) Regulations No. 85/2003."

2. *Amendment*

The Emergency Relief Transport Enterprise Council of Ministers Regulations No. 21/1997 is hereby amended as follows:

Article 5 is deleted and replaced by the following new Article 5:

"5 *Capital*

The authorized capital of the enterprise is Birr 58,318,755.83 (Fifty eight million and three hundred eighteen thousands and seven hundred fifty five birr and eighty three cents) which is fully paid up in cash and in kind."

፫· <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ መጋቢት ፲፪ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም

መለስ ዜናዊ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

3. *Effective Date*

These Regulations shall come into force on the date of their publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 21st day of March 2003.

MELES ZENAWI

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC
OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE